# እናት ሰንበት ትምህርት ቤት

አንዳንድ ጊዜ ‹ትምህርት ቤት› የሚለው ሐረግ ሰንበት ትምህርት ቤትን አይገልጻት ይሆን ብዬ አስባለሁ፡፡ ‹ሰንበት ትምህርት ቤት› ከምትባል ይልቅ ‹የሰንበት ቤተሰብ ቤት› ብትባል ይሻል ይኾን?

የቤተሰባዊነት ስሜት ለአገልጋዮች እጅግ አስፈላጊ ነው፡፡ ሐዋርያት እርስ በእርሳቸው ‹ወንድሞች› ይባባሉ ነበር፡፡ ወንድሞች መባባላቸው ከአንድ እናትና አባት ተወልደው አይደለም፤ እንዲሁ አገልግሎት የጋራ እናታቸው ሆናቸው ነው እንጂ፡፡ የሳቱትን እንኳን ‹ቢፅ ሐሳውያን (ሐሰተኛ ወንድሞች)› ይሉ ነበር፡፡

ይህንን ቤተሰባዊነት ለማጉላት እኔ ባደግኩባት ሰንበት ትምህርት ቤት የቤተሰብ ጉባኤ የሚባል ጉባኤ አለ፡፡ በዚያ ቀን የሚከወነው እንደ ቤተሰብ ቤተሰባዊና መንፈሳዊ ወጎችን እንዲሁ ሲጨዋወቱ መዋል ነው፡፡ የሰንበት ትምህርት ቤቱ ሰብሳቢ ‹ሰብሳቢ› ሳይሆን ‹አባት› ይባላል፡፡ ኹሉም ‹አባታችን› እያለ ይጠራዋል፡፡ የቀድሞ ሰብሳቢ ‹አያታችን› ይባላል፡፡ ከእርሱ የቀደመው ‹ቅድመ አያታችን› ይባላል፡፡ የአመራር አባላት ወንዶቹ ‹አጎቶች› ሴቶቹ ‹አክስቶች› ይባላሉ፡፡ ሌላው አባል በሙሉ ‹ልጅ› ነው፡፡

ይህ ስሜት ኹሉም ሰንበት ትምህርት ቤት ውስጥ አለ፡፡ ሰንበት ተማሪ ዘመደ ብዙ ነው፡፡ አያድርስበትና አንድ ችግር በእርሱ ወይም በቤተሰቡ ላይ ቢደርስበት የእናት ሰንበት ትምህርት ቤቱ ወንድሞቹና እኅቶቹ ነቅለው ቤቱ ይሔዳሉ፡፡ ታምሞ ከሆነ ቤቱን ሞልተው ፣ ውዳሴ ማርያምን አድርሰው ዘምረው ያበረቱታል፡፡ ኃዘን ገጥሞት ከኾነ እስኪጽናና ከቤቱ አይለዩም፡፡ ዕድርተኛው ‹ጉድ› እስኪል ድረስ ድንኳን የሚተክሉት ፣ ወንበር የሚደረድሩት ፣ ግቢ የሚያጸዱት ፣ ዕቃ የሚያጥቡት የሰንበት ትምህርት ቤት እኅትና ወንድሞቹ ናቸው፡፡

ባለቤቱ እንዲደረግ የፈለገውንና የሚያስፈልገውን በማድረግ ልቡን በእርካታ ይሞሉታል፤ እንደ ልቡ ይሆኑለታል፡፡ የዮናታን ጋሻጃግሬ ለዮናታን እንዳለው ‹‹እንዳንተ ልብ ሁሉ የኔም ልብ እንዲሁ ነው›› ብለው የልባቸውን መሻት ከወዳጃቸው ልብ መሻት ጋር አንድ ያደርጉታል፡፡ (1ሳሙ. 14፥7)፡፡ እርሱ ሲያዝን የእርሱ አፍ ሳይኾን የራሳቸው ልብ ይነግራቸዋል፤ ‹እንደርሱ ልብ ሁሉ የእነርሱም ልብ እንዲሁ ነውና›፡፡

ሰርግ ካለበትም የሥጋ ቤተሰቡ አብዝቶ መጨነቅ የለበትም፡፡ በጎደለው ኹሉ የመንፈስ ቤተሰቦቹ አሉለት፡፡ ምናልባትም ልጅየው ብዙ ጊዜውን ለሰንበት ትምህርት ቤት በመስጠቱ የሚበሳጭ ቤተሰብ ቢኖረው እንኳን ከእንደዚህ ዓይነት ገጠመኝ በኋላ ኹሉም ነገር ይለወጣል፡፡ የወንድሞቹና የእኅቶቹ መተሳሰብ፣ የሚቃወም ልቡናን ኹሉ በፍቅር ሊያነድ የተቀጣጠለ ስንዱ እሳት ነው - ‹‹ፍቅር የኃጢአትን ብዛት ይሸፍናል›› እንዲል፡፡ (1ጴጥ. 4፥8)፡፡

የሰንበት ትምህርት ቤት ወንድሞች እውነተኛ ወንድሞች ናቸው - በፍቅር የተገመደ ትሥሥር ያላቸው፡፡ ወንድማቸው ሲበርደው እነርሱ የሚንቀጠቀጡ ፣ ሲርበው አንጀታቸው የሚላወስ ፣ ሲከፋው አብረው የሚያለቅሱ ውድ ወንድሞች ናቸው፡፡ ለእኅታቸው ድጋፍን ከመስጠት የማይሰንፉ ፣ ታናሻቸውን በትምህርት የሚረዱ ፣ ለጥያቄዎቹ የማይሰለቹ ልበ ወርቆች ናቸው፡፡ አብረው መብላት ፣ መጎራረስ ፣ አብረው ማደግ ፣ አብረው መሳቅ ፣ አብረው መጫወት ፣ አብረው መሔድ ፣ አብረው ማንበብ ፣ አብረው መኖር የሚያጓጓቸው የኅብረ ስልቻዎች ናቸው፡፡ የሰንበት ትምህርት ቤት ወንድሞች በሰንበት ትምህርት ቤት እንጂ በየትም በሌላ ቦታ አይገኙም፡፡

የሰንበት ትምህርት ቤት ወንድሞች እንደ ዮናታን ናቸው፡፡ ዳዊት ጎልያድን ገድሎ በዮናታን አባት በንጉሡ በሳኦል እልፍኝ ከተገኘና የራሱን ማንነት ለንጉሡ ካስረዳ በኋላ ‹‹የዮናታን ነፍስ በዳዊት ነፍስ ታሠረች፥ ዮናታንም እንደ ነፍሱ ወደደው›› (1ሳሙ.18፥1)፡፡ ዮናታን ዳዊትን እንደ ነፍሱ ስለ ወደደው አባቱ ሳኦል በጠላትነት ሲነሣበት እንኳን እንደ ነፍሱ የወደደውን ዳዊትን ከአባቱ በምክሩ ይደብቀው ነበር፡፡ የሰንበት ትምህርት ቤት እውነተኛ ወንድሞችም እንዲሁ ናቸው፡፡ ዳዊት የተባሉ አዳዲስ አባላት ጎልያድ የተባለ ከአገልግሎት መራቅን ድል ነሥተው ወደ ሰንበት ትምህርት ቤት ሲመጡ ነፍሳቸው በዳዊቶቹ ነፍሶች ትታሰራለች፣ እንደ ነፍሳቸውም ይወዷቸዋል፡፡ ምንም ዓይነት ‹ሳኦል› ቢመጣ ከዳዊቶች ጎን ይቆማሉ፡፡ እንዲህ ዓይነት ወንድሞች በሰንበት ትምህርት ቤት ወይም የሰንበት ትምህርት ቤት ልብ ባላቸው ዘንድ እንጂ በየትም በሌላ ቦታ አይገኙም፡፡

የሰንበት ትምህርት ቤት እኅቶች ትሕትና የቀበራቸው ፣ ሃይማኖት ያስጌጣቸው ፣ ቅንነት ያቆነጃቸው ፣ የፍቅር ኩራዞች ናቸው - ፀሐዩአ ለጠፋባት የሴትነት ዓለም ክራቸው እየተቃጠለ ብርሃንን የሚለግሱ ፣ እየጨሱ መቅረዝ የኾኑ፡፡ ወንድሞቻቸውን የሚያከብሩ ፣ ለሥርዐተ ቤተ ክርስቲያን የሚታመኑ ፣ ካህናትን ሲያዩ ልባቸው በሚገባ ፍርሐትና አክብሮት የሚርድ የሀገር ኩራቶች ናቸው፡፡ ወንድሞቻቸውን አጥብቀው የሚሹ የቤተሰቡ የወርቅ ምሰሶዎች እነርሱ ናቸው፡፡ በብዙ ትግልና ልፋት ወደ ሰንበት ትምህርት ቤት ይመጣሉ፤ ሰማይ የሚያክል ጫናን አገር የሚያክል ጾታዊ ተፅዕኖን ተቋቁመው ያገለግላሉ፡፡ የሰንበት ትምህርት ቤት እኅቶች በሰንበት ትምህርት ቤት እንጂ በየትም በሌላ ቦታ አይገኙም፡፡

የሰንበት ትምህርት ቤት እኅቶች እንደ አቢጊያ ናቸው፡፡ የናባል ሚስት አቢጊያ ባሏ ንጉሡን እስከ መዳፈር የደፈረ እጅግ አስቸጋሪ ሰው ነበር፡፡ ንጉሥ ዳዊትም እርሱን ሊገድለው ሲሔድ ብልኋ አቢግያ በመንገድ ጠብቃ ንጉሡ ይቅርታ ያደርግለት ዘንድ በብዙ ትሕትናና እጅ መንሻ ለመነችው፡፡ ዳዊትም አቢግያን አደነቀ፤ ‹‹ወደ ደም እንዳልሄድ፥ በእጄም በቀል እንዳላደርግ ዛሬ የከለከለኝ አእምሮሽ የተመሰገነ ይሁን፥ አንቺም የተመሰገንሽ ሁኚ›› አላት፡፡ (1ሳሙ.25፥33)፡፡ የሰንበት ትምህርት ቤት እውነተኛ እኅቶችም እንደ አቢጊያ ናቸው፡፡ ሰውን ከክፋት በመመለስ ፣ በእርጋት ፣ በትሕትና ፣ በአስተዋይነት አዕምሮአቸው የተመሰገነ፡፡ ሰውን ኀትተው ወደ ስሕተት የሚከቱ አሰናካይ ሴቶች በበዙበት በዚህ ዘመን ብልጭልጭን ንቀው የሚስተውን የሚመልሱ የተመሰገኑ ናቸው፡፡ ስለ ወንድሞቻቸውና ስለ እኅቶቻቸው አብዝተው የሚጨነቁና የሚጸልዩ ፣ ጸብን ለማራቅ ዘወትር በብልኃት የሚመክሩ ፣ ‹ልታይ› ከሚሉት ጀርባ የሚገኙ ባለ ምስጉን አዕምሮዎች ናቸው፡፡ እንዲህ ዓይነት እኅቶች በሰንበት ትምህርት ቤት ወይም የሰንበት ትምህርት ቤት ልብ ባላቸው ዘንድ እንጂ በየትም በሌላ ቦታ አይገኙም፡፡ እኔ በግሌ ልጅ እያለሁ እነዚህ እኅቶችና ወንድሞች ዕቅፍ አድርገው ተቀብለውኝ ወንድማቸው ባያደርጉኝ ኖሮ አሁን ያለው ማንነቴ አይኖርም ነበር፡፡ ለመጀመሪያ ጊዜ ሰንበት ትምህርት ቤት ስገባ በፍቅር ሸማ ፣ በመውደድ ብሉኮ ያከናነቡኝን ፣ በጉጉት የተቀበሉኝን ውድ የኆኅተ ብርሃን ቤተሰቦቼን የልጅነት አዕምሮዬ አይዘነጋቸውም፡፡ እነዚህን ወንድሞችና እኅቶች በሰንበት ትምህርት ቤት እንጂ በሌላ በየትም ቦታ እስካሁንም አላገኘኋቸውም፡፡

ሰንበት ተማሪ ሌላ ሰንበት ተማሪን በመንገድ ሲያገኝ ወይም በአጋጣሚ ሲተዋወቅ የጠፋ የእናቱን ልጅ እንዳገኘ ልቡ በፍቅር ስስት ይቃጠላል፡፡ ኹለት የማይተዋወቁ ሰንበት ተማሪዎች ቢገናኙ ለመግባባት ጊዜ አይወስድባቸውም፤ ልቡናቸው ቀድሞ ይግባባል፡፡ ስማቸውን እንኳን ሳይተዋወቁ ስለ መስቀል ጥናት ፣ ስለ ጥምቀት ፣ስለ ደብረ ታቦር ፣ ስለ ፍልሰታ ፣ ወዘተ… ያወራሉ፡፡ አባባሉስ ቢሆን ‹‹አንድ ዓይነት ላባ ያላቸው ወፎች በአንድነት ይበራሉ - Birds of the same feather fly together›› አይደል የሚለው?

ታክሲ ውስጥ ከጎን የተቀመጠው ሰው ሐመር ወይም መለከት መጽሔትን ከያዘ አለበለዚያም አንድ መንፈሳዊ መጽሐፍን እያነበበ ከኾነ ሰንበት ተማሪ አያስችለውም ‹‹ወንድሜን (እኅቴን) አገኘሁ›› ብሎ ሊያወራ ይቋምጣል፡፡ በክርስቲያናዊ አለባበስ ያሸበረቀችና አካሏን ከመራቆት የሸፈነች ‹እኅቱን› ካየም እንደዚያው፡፡ ሌላው ይቅርና አንገቱ ከክር ያልተራቆተ ሰውን ማግኘት ራሱ እንዴት እንደሚያስደስተው!

ሰንበት ተማሪ ‹ሰንበት ትምህርት ቤት› የተባለች ውድ እናት አለችው፡፡ ብዙ ወንድሞችና እኅቶችን የሰጠችው ይህችው እናቱ ናት፡፡ እርሷ ስትነካበት አይወድም፡፡ ሰንበት ተማሪ ሳይሆኑ ፣ የሰንበት ትምህርት ቤትን ቁስል ሳያውቁ ፣ በችግሯ ሳይቸገሩ ፣ በደስታዋ ሳይፈነጥዙ ፣ ጣዕሟን ሳያጣጥሙ ፣ መዐዛዋን ሳያሸቱ ፣ አካሏን ሳይዳስሱ ፣ ቁመናዋን ሳይመለከቱ እንዲያው በሩቁ ብቻ ገምተው የሚተቿት ሰዎች እጅግ ያበሳጩታል፡፡ ምን ዓይነት ተጽዕኖ እንዳሸመደመዳት ፈጽሞ ሳይረዱ ‹‹ለምን እንዲህ አትሆኑም›› የሚሉ ያቃጥሉታል፡፡ በአንጻሩም የእናቱን ዕድገት የሚሻ ነውና በፍቅር ቀርበው ‹‹ለምን እንዲህ አታደርጉም›› የሚሉትን እጅግ ያከብራል፡፡ ‹‹ምን እናግዝ›› ብለው አብረው ለማገልገል የሚፈቅዱትን እጅግ ይወዳል፡፡ እናቱን ካለ ምክንያት የሚተችና ዕድገቷን የማይፈልግ ከራሱ ወንድሞች እንኳን ቢነሣ ቁጣው ብርቱ ነው፡፡ የሰንበት ተማሪ የዘወትር ጥሪው ‹‹ኑ ኹላችንም በእናት ቤተ ክርስቲያን ጥላ ሥር አንድ ቤተሰብ እንሁን፤ እናት ሰንበት ትምህርት ቤትንም እንደግፍ›› ነው፡፡

እናት ሰንበት ትምህርት ቤት ለዘለዓለም ትኑር!

በዲያቆን ሕሊና በለጠ